# አብዮታዊ ዴሞክራሲ፣ ጥገኛው ሃይልና
# የመለስ ራዕይ

(ክፍል አንድ)

ዮናስ 11/09/12

ቀደም ባሉ አገዛዞችና ሥርዓተ መንግሥታት የኢትዮጵያ ህዝቦች ለዴሞክራሲ እውን መሆን ሲታገሉ ዘመናት ተቆጥረዋል። ይልቁንም በአገራችን ጠንካራ ማዕከላዊ መንግስት ከተመሰረተበት 19ኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያ ጀምሮ የኢትዮጵያ ህዝቦች ለዴሞክራሲና ለዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስልጣን በተለያየ ደረጃና በተለያየ አኳኋን ታግለዋል። በአገራችን የዴሞክራሲያዊ ፖለቲካ ስልጣን ጥያቄ ከብሄሮች መብትና እኩልነት፣ ከኢኮኖሚያዊ እኩልነት በተለይም ከመሬት ጥያቄ ጋር ሊነጣጠል በማይችል አኳኋን የተሳሰረ ሆኖ ኖሯል። ስለሆነም የኢትዮጵያ ህዝቦች የዴሞክራሲ ትግል ከህዝቦች ዴሞክራሲያዊ አንድነት፣ ከብሄር ብሄረሰቦች እኩልነት፣ ከመሬትና ከኢኮኖሚያዊ እኩልነት ጥያቄ ጋር ተዳብሎ ተካሂዷል።

ይህ ትግል እጅግ በጣም በተወሳሰበና ጠመዝማዛ ሂደት ውስጥ ካለፈ በኋላ ከደርግ ስርዓት ውድቀት ወዲህ እውን በሆነው አዲሱ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግቡን ሊመታና ዴሞክራሲ በአገራችን እውን ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር ችሏል። ባለፉት 21 ዓመታት በአገራችን ዴሞክራሲን፣ ዴሞክራሲያዊ አንድነትን እና ኢኮኖሚያዊ እኩልነትን እውን ለማድረግ የተከናወነው ትግል ለአገራችን የአዲስ ታሪክና ምዕራፍ በር ከፋች ሆኗል።

ህዝብን ለማገልገል ቆርጦ የሚነሳ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ምሁር የመኖሩን ያህል፣ ለስልጣን ባለው ቅርበት የጥገኝነት አጋፋሪ መሆን የሚፈልግ ምሁርም ይኖራል። ይህ ጥገኛ ምሁር በመንግስት የተለያዩ የስልጣን አካላት ውስጥ የሚገኝ ብቻ አይደለም። ይልቁንም የመንግስት ስልጣን በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ሂደት ላይ ለእንደነዚህ አይነት ሰዎች የማይመች እየሆነ በሄደ ቁጥር ከመንግስት የስልጣን አካላት ውጪ ያለው ምሁር ዋነኛው የጥገኛ ምሁር ምንጭ እየሆነ ይሄዳል።

ለዚህም አቢይ ማሳያ ሊሆኑን የሚችሉት አንዳንድ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሲሆኑ ጥገኛው ምሁር እነዚህን ተቋማት በመጠቀም የመክበር እድሉ የሰፋ በመሆኑ ተቋማቱ የጥገኛው ምሁር ቁልፍ መሸሸጊያና መፈልፈያ ሆነው ተገኝተዋል። በዚህና በመሳሰሉ አገራዊ ጥያቄዎች ላይ ተቋማቱ የነበራቸው አሉታዊ ተጽእኖ እየሰፋ በመሄዱና ለሚደረገው የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ እንቅፋት እየሆኑ በመምጣታቸው የተዘጋጀውን መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አዋጅ

በመጀመሪያው ረድፍ ላይ ተሰልፈው ሲቃወሙ የነበሩት እነዚሁ ጥገኛ ምሁራን መሆናቸውም ሁለተኛው ማሳያ ነው።እነዚህ ሃይሎች በራሳቸው ያላመጡትና ግን ደግሞ ፍላጎታቸውን ሊያሳካና የፀረ ዴሞክራሲያዊ ህይወታቸውን የሚያቀይላቸው ሌላም ተጨማሪ ሃይል እንዳላቸው መገንዘብ ያሻል ።

ፀረ ዴሞክራሲ፣ ጥገኝነት ገመናውን ገልጦ በመቅረብ ከህዝብ ተቀባይነት ሊያገኝ እንደማይችል የሃገራችን ነባራዊ ሁኔታ ያረጋግጣል። እንደምንም ስልጣን ይዤ ለመክበር አስቤያለሁና ምረጡኝ ብሎ የህዝብን ድጋፍ ማግኘት እንደማይችልም ይገነዘባ፡፡ ምንም እንኳ በሰበሰባት ብር መሬት ገዝቶ እያከራየ መኖርን ስለሚፈልግ መሬት እንዲሸጥ ቢፈልግም ይህ ጉዳይ ቢያንስ በአርሶ አደሩ አካባቢ ተቀባይነት ሊኖረው ስለማይችል ዋነኛ መከራከሪያው አድርጎ ሳይሆን በገደምዳሜው ያቀርበዋል።

ሌላው ቀርቶ በባህሪው ፀረ ዴሞክራሲን እቃወማለሁ ብሎ ሊቀርብ እንደማይችል ይታወቃል። ስለሆነም የግለሰብ መብቶችን ከቡድን መብቶች ነጥሎ ለግለሰብ መብት የቆምኩ ነኝ ማለት ተቀባይነት ስለሚያሳጣው የብሄር/ ብሄረሰቦችን መብት በተሸፋፈነ አኳኋን ለመቃወም ሲገደድ ይታያል፡፡ ጥገኛነት ሃቀኛ ማንነቱን በማስረዳት መጠናከር ስለማይችል ይህንኑ በመሸፈን የህዝቡን ድጋፍ ሊያገኝ የሚችልበት እድል መሻት ይኖርበታል። በዚሁ መሰረት የታዳጊ ስርዓቱን ጉድለቶችና በህዝቡ ውስጥ ያሉ ጥገኛና ኋላቀር አመለካከቶችን በዋና ሃይልነት ፈርጆ እነዚህን በመጠቀም የሚጠናከርበትን መንገድ መሻት አለበት። እነዚህ ሃይሎች ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ሞት በኋላ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓቱን በፀረ ዴሞክራሲያዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚ ለመተካት የሚያስችለውንና ከስልጣን ሽግግሩ ጋር የተያያዙ መፈክሮችን ሲያሰሙ ቆይተዋል።

ከመለስ ሞት በኋላ ሊበታተን ይችላል ተብሎ በነዚሁ ጥገኛ ሃይሎች የተሟረተበት ኢህአዴግ የበለጠውኑ ጠንክሮና ጎልቶ በመውጣቱ የተበሳጨው ፀረ ዴሞክራሲ ሃይል ከላይ በተጠቀሰው ታክቲኩ መሰረት የበሬ ወለደ የስልጣን ሽኩቻ ታሪኮችን ከመለፍለፍ ጀምሮ በዚያው በኢህአዴግ ውስጥ ተወልደው በተሃድሶው ወቅት የተቀረጡትን የትምክህትና የጥገኝነት አስተሳሰቦችን በማራገብ በየብሄራዊ ድርጅቱ መከፋፈልና ልዩነት ይፈጠር ዘንድ ያለውን ከንቱ ምኞት በማስተጋባት ላይ ተጠምዷል፡፡

አብዮታዊ ዴሞክራሲ፣ ልማታዊ መንግስትና የመለስ ራዕዮች ደግሞ የዚህ ሃይል ዋና ማቀንቀኛዎቹ ናቸው። ይህ ሃይል ቀድሞም ቢሆን የሚፈጠሩ ክስተቶችን እና ሁነቶችን እየተከተለ በማራገብ፣ ከጸረዴሞክራሲ ሃይሎችና ኪራይ ሰብሳቢዎች የሚላክለትን ድጎማ እየተቀበለ የተባለውን ያደርግ ዘንድ ፈቅዶ የገባ እንደሆነ በርካታ ማሳያዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ቀደም ሲል የሊዝ አዋጅ ፣ የግብር ስርዓት ፣ ዋልድባና ጉራፈርዳ፣ የአወልያው ጉዳይ የሚሉን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከአቶ መለስ ሞት በኋላ የተገኘውና እንደምቹ አጋጣሚ በዚህ ሃይል የተወሰደው ደግሞ ሰላማዊውን

የስልጣን ሽግግር የጥበትን እና የትምክህትን ካባ ማልበስ ሲሆን ምንም እንኳን እነሱ ቢያሚርቱም በሰላም የተጠናቀቀውን የመጅሊሱን ምርጫ ደግሞ እንደአቀጣጣይ ቤንዚን መጠቀም ነበር።

ፍትህ ጋዜጣ ከተቋረጠች በኋላ ፎጣ ጠምጣምያን የሆኑት የፍትህ አዘጋጆችና አምደኞች በአዲስ መልክ "ተመልሰናል" ሲሉ አዋጅ አስነገረው "አዲስ ታይምስ" የሚል የመጽሄት ስያሜ በመያዝ የውዥንብር፣ የጭፍን ጥላቻና የከፋፋይ ፖለቲካ ዘመቻቸውን ቀጥለዋል። በዚህች መጽሄት ያልተገደቡቱ እና "ነፃ ጋዜጠኞች" ነን በማለት ሌት ተቀን የሚያወሩት እነዚህ ፎጣ ጠምጣሚያን በይፋ የሰማያዊ ፓርቲ ልሳን ለሆነችው ሰማያዊ መጽሄት ዋና አዘጋጅ እስከመሆንና ከዚህም አልፈው በፓርቲ አመራርነት ጭምር እየተሳተፉ ያሉበት ሁኔታ እየተስተዋለ ሲሆን ዴሞክራሲያዊና ልማታዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚን በፀረ ዴሞክራሲያዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚ ለመተካት ታዳጊ በሆነ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ጥቃቅንና ጊዚያዊ ችግሮችን በማጉላት "ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ" እንዲሉ ከራሳቸው አልፈው ህዝቡን ለአደባባይ አመጽ ጭምር እየጠሩና "አትነሳም ወይ" እያሉ ሰይጣናዊ መለከታቸውን በመንፋት ላይ ናቸው።

ስለሆነም በመጣጥፌ መግቢያ ላይ ለመጠቆም እንደሞከርኩት ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጽንሰ ሃሳብና ከሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ፣ ከአብዮታዊ ፎጣ ጠምጣምያን እና ከፀረ ዴሞክራሲ ሃይሎች አሰላለፍ አንፃር ቅኝቴን ከጥቅምት 2005 ቅጽ 2 ቁጥር 7አዲስ ታይምስ መጽሄት እጀምራለሁ።

የሃሳቤ መነሻ የመጽሄቷ ማኔጂንግ ዳይሬክተር የሆነው ተመስገን ደሳለኝ ነው። በነገራችን ላይ "አዲስ ታይምስ" መጽሄት ከመሆኗ በዘለለ በይዘቷ ከፍትህ ጋዜጣ ያልተለየች፣ አምደኞቿና አዘጋጆቿም እነዛው የፍትህ የነበሩት ስለመሆናቸው ተመስገን በ"ተመልሰናል" የአዲስ ታይምስ መጽሄቱ 5ኛ እትም ማረጋገጡን ቀደም ብዬ ጠቅሻለሁ፡፡ ነገር ግን መጽሄቷ ሌላኛዋ ፍትህ ከነበረች ተመስገን ስለምን ከዋና አዘጋጅነት ወደማኔጂንግ ዳይሬክተርነት የስራ መደብ ተዘዋወረ? በሚለው ጉዳይ ላይ ወደፊት የምመለስበት እንደሆነ አስታውሼ ከላይ በተጠቀሰው ቀን ለገበያ ወደበቃችው አዲስ ታይምስ ላምራ፡፡

የመጽሔቱ የሽፋን ገጽ የተመስገንን "ኢህአዴግ ስንት ቦታ ሊሰነጠቅ ይችላል?" መጣጥፍ ገና ከመነሻው መልስ እንዲሰጥ ሆኖ የተዘጋጀ ነው፡፡ በአራት ብሄራዊ ድርጅቶች የተዋቀረውን ግንባር መለያ አደማምቆ የድሉን ችቦ አራቱ ብሔራዊ ድርጅቶች ሲቧጨቁት ያሳያል፡፡

ተመስገን በዚህ መጣጥፉ የኢህአዴግና የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ተፈጥሮ በራሱ እነዚህን አራት ብሔራዊ ድርጅቶች የማያግባባና ለብተና የሚዳርግ እንደሆነና "የመለስን ራዕይ" እናስቀጥላለን የሚሉት የግንባሩ አመራሮችም ራዕያቸውን አልተገነዘቡም በማለት ይገልጻል፡፡ በማያያዝም "የመለስ ራዕይ ለአዲስ ዙር የሥልጣን ዘመን መብቃትና ይህንኑም ደኢህዴንን ከፊት አሰልፎ ኦሮሚያን ስልጣን በመንፈግና ህወሃት ከኋላ ሆኖ መዘወር የሚችልበትን ስርዓት መዘርጋት ነው" ይላል፡፡

ለዚህ የሚያቀርባቸው ምክንያቶች ደግሞ የጠቅላይ ሚኒስትር መለስን ሞት ተከትሎ የተከናወነውን የሥልጣን ሽግግር ነው፡፡ ከቤተ መንግስቱ የስራ ኃላፊዎችና በመንግስት በኩል ምንም አይነት መግለጫ ባልተሰጠበትና ሚዛኑን ባልጠበቀ የይሆናል አሉባልታ በመነሳት ወ/ሮ አዜብ ከቤተመንግስት አልወጣም እንዳሉ በማስመሰል ፀረ ዴሞክራሲያዊ መርዙን ለመርጨት ይዳክራል፡፡ በማያያዝም "ሀገሪቷ በህግ የማትመራና አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትርም ጥርስ የሌለው አንበሳ ተደርገው መሰራታቸውን የሚያረጋግጥ ነው" ይለናል፡፡

ይህንኑ ምንጭ አልባና የሃሜት ፖለቲካ መሰረት ያደረገው ተመስገን ሲቀጥል፦ ኦህዴድ ያደረገውን ግምገማና የአቶ ጁነዲን ሳዶን ከድርጅታዊ ሃላፊነት መውረድ በማውሳት፣ የኦህዴድ አባላቶች ጠቅላይ ሚኒስትር  የመሆን እድል ለምን ሊነፈጋቸው ቻለ? ሲል ጠይቆ ከፋፋይ የሆነውን ፀረ ዴሞክራሲያዊ ምላሽ በመስጠት፣ ወ/ሮ አዜብ "የመለስ ራዕይ ሳይበረዝ እንዲቀጥል እፈልጋለሁ፣" ያሉትን በማስታወስ ከህወሃት አልያም ከኦህዴድ አካባቢ መፈንቅለ መንግስት ሊነሳ የማይችልበት ምክንያት አይኖርም በማለት የራሱን የከንቱ ምኞት ድምዳሜ ያቀርባል፡፡

ይህንን ሃሳቡን ”  “የመለስ ራዕይ” ከውስጥ እንጂ ከውጭ ለሚነሳ የፖሊቲካ ልዩነት መድሃኒት የመሆን አቅም የለውም፡፡ ስለዚህም በአራቱ ድርጅቶች (ህወሃት፣ ብአዴን፣ ኦህዴድ እና ደኢህዴን) መካከል ወይም በታጠቀው ሃይል የመጠቀም ችሎታ ያለው ቡድን በኢህአዴግ ውስጥ ልዩነት ይዞ ቢወጣ የግንባሩ እድል ፈንታ የመጨረሻ ከመሆን የሚታደገው አይኖርም” ሲል በመሰረተ ቢስ ትንተናው  ያልበላውን ማከኩን ይቀጥላል፡፡

በሌላም በኩል ወ/ሮ አዜብ የኤፈርት ስራ አስኪያጅ ባልሆኑበት ተጨባጭ ሁኔታና የፕሬዝዳንት ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ የስልጣን ዘመን አንድ አመት እየቀረው "አብቅቷል" በማለት በቅዠት ህልሙን ያየውን "የስርዓቱን የመዳከምና የመከፋፈል አደጋ" ሊነግረን ሞክሯል፡፡ እዚህ ላይ የተመስገንን ፀረ ዴሞክራሲያዊ አካሄዶችና የጥገኛነት መፈክሩን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአብዮታዊ ዴሞክራሲን ጽንሰ ሃሳብና የመለስን ራዕይ ያልተረዳበትን መንገድና የመስመሩን ጥንካሬ ከሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታና ከመስመሩ ታሪካዊ ዳራ  በመነሳት አንዳንድ ሃሳቦችን ማንሳት ጠቃሚ ይሆናል፡፡

በዚሁ መሰረት ስለ ስርዓተ መንግስቱና የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚ፣እንዲሁም ስለ ፀረዴሞክራሲው ሃይል ስናወሳ የስርዓተ መንግስቱ መሰረት እና የማእዘን ድንጋይ ስለሆነው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመርና አሰላለፍ እንዲሁም ስለፀረ ዴሞክራሲው ሃይል አሰላለፍና መሰረት ስለሆነው የትምክህትና የጥበት መፈክር ማንሳት ግድ ይለናል፡፡ በመግቢያዬ አካባቢ ጉዳዩን በተመለከተ ጥቂት ነገር ያነሳሳሁትም  ለዚሁ ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ  ሆኖ  የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመርንና የፀረ ዴሞክራሲውን ሃይል መፈክር ከተመስገን መጣጥፍ ጋር በማዛመድ እዚህ ጋር መመልከቱ ርዕሰ ጉዳያችንን የበለጠ ግልጽ ያደርግልናል፡፡

የፀረዴሞክራሲው ሃይል መፈክር የሆኑት የትምክህትና የጥበት አስተሳሰብ በባህሪያቸው በአንድ አካባቢ ብቻ የታጠሩና የዚህኛው ወይም የዚያኛው ብሄር መሰረታዊ መገለጫ ሳይሆኑ በሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች አካባቢ ያሉና የሚስተዋሉ ጉዳዮች ናቸው፡፡ የሚለያዩበት ጉዳይ ቢኖር የመልክ ብቻ ነው፡፡ ትምክህተኛው ያረጀ ያፈጀ የፀረ ዴሞክራሲያዊ ኢትዮጵያዊነት ፍፁምነት መፈክር ይዞ ሲነሳ ጠባቡ ደግሞ ኢትዮጵያን የመነጣጠል አጀንዳ ይዞ ይነሳል፡፡ በዚህም ምክንያት በፍፁም የማይጣጣሙ ሁለት ጫፎች ሆነው ሊታዩ ይችላሉ፡፡ በርግጥም በሁለቱ ጥገኛ ሃይሎች መካከል ቅራኔ መኖሩ ያለና ለወደፊቱም የሚኖር ጉዳይ ቢሆንም ሁለቱም ከአንድ ምንጭ፣ ከጥገኝነት ምንጭ የተቀዱ በመሆናቸው መሰረታዊ ይዘታቸው አንድና ያው ነው፡፡ ፀረ ዴሞክራሲያዊውን ሃይል ወደ ስልጣን ማምጣት፡፡

ትምክህተኝነቱን እና ጥገኝነቱን እንደ አስፈላጊነቱና እንደ አመቺነቱ ለመጠቀም ደግሞ ጥገኛ የሆኑ የኦሮሞ ምሁራን  እና በፀረዴሞክራሲ መስመር የተሰለፉ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን፤ ትምክህተኛ የሆኑ የአማራ ምሁራንን እና የአንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን በመረጃ ምንጭነት እና በአወዳሽነት እየተጠቀመባቸው ነው፡፡ ለዚህም እነ አቶ አስራት ጣሴን ፣ፕ/ር መስፍን ወልደማርያም ፣ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ፣አቶ አሰገደ ገብረ ሥላሴ ፣ኢ/ር ዘለቀ ረዲ የመሳሰሉትን አምደኞችና የመረጃ ምንጮች ናቸው እየተባለ የሚነገርላቸውን ሰዎች እዚህ ላይ ልብ ይሏል፡፡ ከዚህም በላይ አንዱን ብሄረሰብ እንደ አሻንጉሊት ሲመስል፤ ሌላኛውን ደግሞ መፈንቅለ መንግስት አከናዋኝ በማድረግ ስውር ሴራውን ስኬታማ ለማድረግ ይዳክራል፡፡

የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር እና የመለስ ራዕይ አንድና ያው ናቸው፡፡ የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካል አኮኖሚን መድፈቅና የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚን በኢትዮጵያ ምድር ማንገስ፡፡ ህወሃትን ብአዴንንና ኦህዴድን ይዞ ደርግን የደመሰሰው አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ሃይል በደቡብም ተመሳሳይ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ሃይል ፈጥሮ ግንባሩን እንዲቀላቀል ከማድረግም በላይ የመስመሩን ፊታአውራሪዎች ማብቃት ችሏል፡፡

የዚሁ የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ሃይል ስብስብ የሆነው ግንባር ኢህአዴግ የሁሉም ብሄሮች የዴሞክራሲ ሃይሎችን በዴሞክራሲያዊ አላማ ዙሪያ በማሰባሰብ አንዱ የሌላው አጋር በመሆን፤ አንዱ በሌላው ላይ ተማምኖ በጋራ በእኩልነት ሊራመዱ የሚችሉበትን ሁኔታ በመፍጠር ፤የሰላምና የዴሞክራሲ ጎዳና ዋስትና እንዲያገኝ፤ የመበታተንና የእልቂት መንገድ ጨርሶ ላይነሳ እንዲወገድ ያደረገና ዛሬ ላይ የደረሰ ግንባር እንጂ ተመስገን እንደሚያወራው የጥገኞችና ትምክህተኞች መናኸሪያ አይደለም፡፡ ተመስገን እና ሌሎቹም የፀረዴሞክራሲው ካምፕ አባላት መገንዘብ ያለባቸው የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመር ራሱን በራሱ ማረም የሚችል ስርዓት  መሆኑን ነው፡፡

አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመር መጀመሪያ በተቻለ መጠን ስህተቶች እንዳይፈጠሩ መስራት፤በሆነ አጋጣሚ ችግሮች ከተፈጠሩም ሁሉም በሚማርበት አኳኋን ለማስተካከል የሚያስችል የግምገማ፣ የሂስና ግለሂስ ባህል ለግንባሩ ፈጥሮለታል፡፡ ይህ ስርዓት ደግሞ በሂደት እየተገነባና አሁን ለደረሰበት የማይነቃነቅ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ ስለሆነም እነ ተመስገን እንደሚያወሱት የነፈሰው ሁሉ እንደሚበትናቸው የ97ቱ ቅንጅቶችና የመርህ ይከበሩ አንድነቶች ወይም ደግሞ የዶክተር መራራ ጉዲናና የእገሌ ኦብኮ እንደሚባሉቱ አይነት ሳይሆን አብዮታዊ ዴሞክራሲ በህዝቡ ሁለንተናዊ ተሳትፎ በማይናወጽ መሰረት ላይ የተገነባና አመራሩም ለዚሁ መርህ ተገዝቶ በመተራረም ስርዓቱን ለማስቀጠል ሌት ተቀን የሚተጋ እንጂ ምንም አይነት ሽኩቻ ውስጥ የሚገባበት መሰረታዊ መነሻ የለውም፡፡ የመለስ ራዕይን ከሃይለመስቀል በሸዋም የለህ "የሃይለማርያም የርእዮተ –አለም ዕዳ" መጣጥፍ ጋር በክፍል 2 እንመለስበታለን፡፡